# ★ ዴሞክራሲያ ★

* የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ልሳን *

**ዴሞ ቅጽ 39 ቁጥር 5** **መጋቢት 2006 ዓ ም**


## ለእነሱ ጣመ እንጂ እኛንስ ገደለን !

በጥላቻ ተወልዶ ጥላቻን በሀገር ደረጃ ያሰራጨና ሀገርንም ሕዝብንም የጎዳ ያዋረደ ዘረኛ ቡድን አለምንም ጥርጥር ወያኔ ነው። ከደደቢት በፊት በናቅፋ ኢትዮጵያን እንዴት እንደሚያጠፋ ዕቅድ ያወጣና የተለመ ወያኔ ነበር። በርካታዎቹ የወያኔ መሪዎች የአድዋ ፊውዳል ልጆችና ርዝራዦች ነበሩናም ዘውዱን ሸዋ ቀማን የሚለው እምነት መሠረታዊ ቁጭታቸውና አንቀሳቃሽ ሞተራቸውም ነበር ማለት የሚቻል ነው። በተጨማሪ ወያኔም ሆነ ሻዕቢያ ለኢትዮጵያና ለአንድነቷ የሚቆረቆረው አማራ ብቻ ነው የሚል የቅዠት አቋም ስለነበራቸው በአማራው ላይ መረባረቡ ከያኔ የጀመረና እነሆ እሳካሁንም በአማራው ላይ አሰቃቂ ጥቃትን በማድረስ እየተከሰተ ያለ ነው።

የጥላቻው ጉዞ ሲጀመር ወያኔ ያወጣው መርሀ-ግብር ወይም ጦማር በአማራው ላይ (በተለይም በሸዋው አማራ ላይ) የሚያጓራ ነበር። ትምክህተኛ፣ ሐጢያተኛ ...ወዘተ በሚል አማራውን ሲያብጠለጥል የነበረው ወያኔ ያለው መፍትሔ፣ ተገንጥሎ የራስን ነፃ መንግሥት ማቋቋም ነው ሲል ደምድሞ፤ ግቤም የትግራይ ረፑብሊክን መመስረት ነው ብሎ በይፋ ወጣ። በወቅቱ፣ ኋላ ራሳቸውን ኦነግ ብለው በግንጠላና በአማራ ግድያ የሚሰማሩት ለደርግ ያደሩ የነፃ እርምጃና የቀይ ሽብር ቀንደኞች ነበሩ። በትግራይ መሬትም ለኢትዮጵያ አንድነት እንቆማለን ባሉት በኢሕአፓና ኢዲኅ ላይ በሻዕቢያ ተደግፎ ጦርነት ከፈተ። ይህን ጦርነቱን በኢሕአፓ ላይ ዛሬም ቀጥሎበት አለ። ወያኔ በጥላቻ ዘመቻው ወዳጅና አጋር ብሎ--አሁንም ከሻዕቢያ ጋር በመተባባር--ኮትኩቶ ያሳደገው ኦነግን ነበር። በሻዕቢያና ዚያድ ባሬ ድጋፍ ካርቱም ኮበር እስርቤት አጠገብ ቢሮ እንዲከፍት የተደረገው ኦነግ፣ ሳይውል ሳያድር ታማኝነቱን በጸረ አማራ ዘመቻው ገልጿል። ቀይ ሽብር ደርግና አማሮች ኦሮሞዎችን ለመጨረስ የጠነሰሱትና የወሰዱት እርምጃ ነው ብሎ በጽሁፍ ያቀረበው ይህ ኦነግም የወያኔና የሻዕቢያን ሀገር አፍራሽ ዘመቻ ደጋፊና ተባባሪ ሆኖ ቆይቷል። በለንደኑ ጉባዔ--መንግሥቱ ሀገርን አስረክቦ ከፈረጠጠ በኋላ--ኦነግ ለወያኔና ሻዕቢያ ሽፋን ሰጪ ሆኖ ተገኝቶ ለሽግግር መንግሥት ተብየው የወያኔ ቧልትም ተጋብዞ በደርግ ጊዜ የአሶሳን ጸረ አማራ ፍጅት እንዳካሄደው ሁሉ እነበደኖን ደግሟል። የፍጹም ሥልጣን ጥም ያሳበደው ወያኔ ግን የራሱ አሻንጉሊት/መጫወቻ የኦሮሞ ቡድን (ኦሕዴድ የሚባለውን) መስርቷልና ለኦነግ ትዕግስት አልነበረውም--ሳይውል ሳያድር ብዙ ሺዎችን

አስሮ አመራሩን በቦሌ ወደ ስደት ሸኝቷል። በኦሕዴድ አማካኝነትም ከአርባጉጉ እስከዛሬ ጸረ አማራ ፍጅቱን አጧጥፎ ይገኛል። አማራም ኦሮሞም ኢትዮጵያዊ ደም የነበራቸውን እንደ ኢላማ በመውሰድም አማራው ፈጀህ፤ ጨረሰህ የሚለውን ጸያፍ ቅስቀሳ ከማካሄድ አልፎ በተቆረጠ እጅ ላይ ያረፈ የተቆረጠ ጡትን በሀውልት መልክ ገንብቷል። ሕዝብን ከሕዝብ ማጣላቱ መረን የለቀቀ ዘመቻ በተለይም አማራውን ቢያጠቃም--ወያኔዎች የሚፈሩት ሕዝብ ነውና--በአሁኑ ወቅት ከፋፋይና ገዳይ ዘመቻው ኦሮሞውን፣ ሶማሌውን፣ አኝዋኩን፣ ...ወዘተ የሚያጠቃ መሆኑም እየታየ ነው።

ሕዝብን ቀጥቅጦ ለመግዛት መከፋፈልና ማዳከም የመጀመሪያ ሁሉም አምባገነን የሚያውቀው ስልት ነው። ወያኔ በቅድሚያ ሌሎችን ሁሉ በአማራው ላይ አስነሳ። ቀጥሎ ሌሎችንም በተናጠል እያጠቃ በታተነ፤ አዳከመ። የሀገሪቷን ሀብት በእጁ አስገብቷልና በሆዳቸው የገዛቸውም ጥቂቶች አልነበሩም። ጸረ ጥቁር የሆኑ ቀኝና ፋሺስታዊ ድርጅቶች ውስጥ አፍሪካውያን አባል እንደሚሆኑት ሁሉ ሆዳም አማሮችም የወያኔ ተለጣፊና አገልጋይ ሆነው ያደረሱትና እያደረሱ ያሉትም ጉዳት ከፍተኛና መጠቀስ/መወገዝ ያለበትም ነው። ወያኔ ግን ሥርዓቱን ያቆመው በትግራይ ተወላጆች ላይ መሆኑንም መካድ የሚቻል አይደለም። የትግራይ ሕዝብ ሁሉ ወይኗል ማለት ስህተት ቢሆንም በርካታ የትግራይ ተወላጆች ግን የአገዛዙ ተጠቃሚና ደጋፊ ሆነው የወያኔን ዘረኛነት እየተጋሩ መሆናቸውም አከራካሪ አይደለም። ዋና ዋና የሥልጣን ቦታዎች (ፖለቲካዊ ሆነ ኤኮኖሚያዊ)፤ የጦርና ፖሊስ ተቋማት የተያዙት በትግራይ ተወላጆች ነው። ወያኔ ኢትዮጵያን ለማጥፋት ዘመቻውን ሲጀምር የአማራው ሕዝብ ከሥልጣን ፍርፋሪ (ተረፍ መረፍ) ያገኛልና የትግራይና ሌሎች ሕዝቦች ጠላት ነው ያለውን አድሶና ነፍስ ዘርቶ በራሱ ላይ ማስቀመጡ ተገቢና ትክክል ባይሆንም ይህ ዘረኛ ፖለቲካ የትግራይን ሕዝብ ለአደጋ አጋልጦት እንዳለ ደግሞ በገሃድ ይታያል። አደገ ተመነደገ፤ በለጸገ በዴሞክራሲ ፈነደቀ ብለው አጓጉል አሃዛቸውን የሚደረድሩት ወያኔዎች ግን የሚሰጣቸው ሕዝባዊ ትችት "ለእናንተ ጣመ እንጂ እኛንስ ገደለን" ነው። ከሻዕቢያ ጋር በማበርና ትግራይ ትግሪኚን በማስፈን ኢትዮጵያን በጋራ ሊበዘብዙ ያቀዱት ቢከሽፍባቸውም ዛሬ ኢትዮጵያ የምትገዛው ብዙኃኑን በሚወክል መንግሥት ሳይሆን በጥቂቶች የአንድ ክልል ተወላጆች ነው። ከ1983 እስካሁን ማን ከበረ? ማን በሥልጣን ባለገ? ማን በሙስና የሚሊዮን ዶላሮች ባለቤት ሆነ? ማን የሀገሪቷን ኤኮኖሚ ተቆጣጠረ? ማን በለጸገ? ተዘባነነ? ብለን ብንጠይቅ የትግራይ ተወላጆች ወያኔዎች የሚል ነው መልሱ። ለሽፋን ሰጪነት የተኮለኮሉት ሌሎች ከሆዲዎች ሁሉም ታቅፈዋል ለሚለው ቅጥፈት ማደናገሪያ ብቻ የገቡ ናቸው። የሟቹ አምባገነንና ዘመዶቹ፤ ዋና ዋና የወያኔን ትግራዊ ባለሥልጣናትና ዘመዶቻቸውን ዋልጌነትና በሙስና መጨማለቅ ስናጤነው ይህ አለ ያልነው የባለጌዎች አገዛዝ ሁኔታና ይዘት ሐቅ ሆኖ ይገኛል ።

ወያኔ ኢትዮጵያን ከፋፍሎ መግዛት ብቻ ሳይሆን መሬቷንም ለሱዳን ሰጥቷል --አማራውን ለማዳከም፤ ሱዳንን ከጎኑ ለማቆየት፡፡ ለም መሬቶችንም ለባዕዳን በርካሽ አስረክቦ አርሶ አደሮችን ከቀያቸው በግድ አፈናቅሏል። ለኢትዮጵያ የማይመኘው ውርደትና መከራ የለም ቢባል ስህተት አይሆንም። የጎንደርን መሬት ወደ ትግራይ በጉልበት

እንደጠቀለለው ሁሉ የአማራ ክልል የተባለውን ስፋት ለማጥበብና አቅሙንም ለማዳከም እየጣረ ነው። ያደረገው ሁሉ አልበቃ ሲለው ደግሞ ሆዳሞቹን በሉ ተሳደቡ በሚል በአማራው ሕዝብ ላይ ጸያፍ ስድቦችን አዥጎድጉዷል።

ዛሬም ኢትዮጵያ የረሀብና የችግር ሀገር ሆናለች፤ ልጆቿ ይሸጣሉ፤ ወጣት ሴቶቿ ለዘመናዊ ባርነት ይዳረጋሉ፤ ለአቅመ ሔዋን ያልደረሱትም ወደ ሴትኛ አዳሪነት ተገፍተዋል፤ ከግማሽ ሚሊዮን ያላነሱ--አብዛኞቹ ህጻናት ወንዶችና ሴቶች መንገድ አዳሪ ወይም ሽፍንፍን ካስፈለገ የጎዳና ተዳዳሪ ሆነዋል። ከኑሮ ውድነት ተመጣጣኝ የደሞዝ እድገት ያላገኙት አስተማሪዎች፣ ላባደሮች፣ የቢሮ ሠራተኞች ራሳቸውን በቀን አንዴ መመገብ እያቃታቸው መጥቷል። ከሀገሪቱ ሕዝብ ብዛት አብዛኛውን እጅ የያዘው ወጣት በሥራ አጥነት መከራው ሲበዛበት ከአገር ለመውጣት በሚያደርገው ሙከራም ይህ ነው የማይባል መከራ እየደረሰበት ያለና የቀረውም ለጎጅ ባህሎች እጅግ እየተጋለጠ መጥቷል። ወያኔ ሰበብ እየፈጠረ በብዙ ሚሊዮን ወጭ ሹማምንቱን ሰብስቦ በውስኪ ሲራጭ፣ በአ.አ. ብቻ በብዙ መቶ ሺህ የሚቆጠሩ ዜጎቿ ከቆሻሻ ተራ በመመገብ ህይወታቸውን ለማቆየት የሚሰቃዩ የመንገድ ተዳዳሪዎች መኖር ሀገሪቱ የደረሰችበትን አስከፊ ደረጃ ፍንተው አድርጎ የሚያሳይ አሳዛኝ ሥዕል ነው። በገጠር ያለው ሁኔታም የተሻለ አይደለም፤ የትምህርትና የጤና ሥርዓት መሻሻል የሚታያቸው ባዕዳን ብቻ ሆነዋል። የባለሥልጣኖች፤ የወያኔዎች የተቀማጠለ ኑሮና የሕዝብ ድህነትና ስቃይ ሲወዳደር ደግሞ የወያኔ አገዛዝ የመላ ኢትዮጵያ ሕዝብ ጠላት መሆኑ በግልጽ ይታያል። ደርግ የኮታ መንግሥት ይባል እንደነበረው ወያኔም የጉርሻ በብር ከሃምሳ አገዛዝ ቢባል አይበዛበትም።

ያደቆነ ሰይጣን ሳያቀስ አይለቅም ተብሏልና በሶማሊያ እንደታየው በብሔረሰብ ወይም ጎሳ ደረጃ መከፋፈል ውሎ አድሮ ዋናዎች ነን ያሉትንም መልሶ በጎጥና ሰፈር ልጅነት ሳይቀር መፈረካከሱ የሚጠበቅ መሆኑን ዛሬ ከወርቅ ዜጋ ተወለድን ባዮቹ ወያኔዎች በአውራጃዊነትና ጎጠኝነት ሲናጡ ለማየት በቅተናል። ቁንጮአቸው የነበረው ዘረኛ ወደ እንጦርጦስ ከወረደ ወዲህ ጭፍሮቹ በመናከስ ላይ እንዳሉ ድብቅ አይደለም። ቀደምም ቢሆን ወያኔ የአሸአዎች (ማለትም የአድዋ፤ ሽሬና አክሱም) የበላይነት የሰፈነበት ድርጅት ነው ይባል ነበር። ይህም አውራጃዊ ስሜት የሚሉት ገና ድርጅቱ ሀ ብሎ ሲጀምር ሊበታትነው ቃጥቶ ብዙ ህይወትም ጠፍቷል። አሁንም የአድዋ ተወላጆች የበላይነት በሌሎቹ ላይ ያለው ተጽዕኖ በአሉታዊ መልኩ እየታየም ነው። ዋናው አረመኔ ከተለያቸው በኋላ በእርስ በርስ ሽኩቻ ሲናጡ በግጭታችን ጠላቶች እንዳይጠቀሙ በሚል ለመለስ ዜናዊ ጭፍን ሎሌ ሆኖ የቆየውንና በሲዳማ ሕዝብ ፍጅት የሚከሰሰውን፤ ለፖለቲካ ባዳ የሆነውን ግለሰብ ጠቅላይ ሚኒስትር ብለው ሾመው ከጀርባ ይጋልቡት ዘንድ ተገደዋል፡፡ ይህ ግን ቀጣይ የሚሆን ነው ብሎ መገመት አይቻልም። የከረሩ ወያኔዎች ቢጣሉም ቢጋጩም ወያኔያዊ ግባቸውን በጋራ የሚገፉ በመሆናቸው ከመለስ ተጣላን የሚሉት ምን ያህል የድርጅቱን ገበና እስካሁን ደብቀው እንዳሉ ማየቱ ብቻ ይበቃል። በወሳኝነት በማዕከል ቦታ የነበሩት ዓይኔን ግንባር ያርገው ብለው ዝምታን መርጠዋል፤ በ1997 ምርጫም ደንግጠው ከወያኔ ጎን መቆማቸውን ማስታወሱም በቂ ነው። ሆኖም ክፍፍላቸው ያለና የሚቀጥል እንደሆነ ይታወቃል። ባዕዳን በተለይም አሜሪካ በክፍፍላቸው ጣልቃ በመግባት ስልክ ጠላፊና ድረ-ገጽ አጋጅ የሆነው ወያኔ (በዛሬው ምክትል ጠቅላይ ሚኒስቴር) የሚመራውን ቡድን በመደገፍ

ላይ መሆኗ ታውቋል። በአርባ ምንጭ የአየር ኃይል ጦር ሠፈር ለአሜሪካ የለገሰው ወያኔ በአሜሪካ ትዕዛዝ ወደ ሶማሊያ ጦር ልኮ ዜጎችን በማስፈጀትና ሶማሌዎችንም በመግደል ላይ ነው፡፡ ይህ ድጋፍን ያስከተለለት ሲሆን፣ በሌላ በኩል የአሜሪካና የቻይና ፉክክርም ወያኔዎቹን እርስ በርስ እያቃረናቸው መሆኑ ይታያል። ከመድረክ የተገለሉትም በጠንካራ ወኔ ባይታሙም መፍጨርጨራቸው የሚጠበቅ ነው። ይህን ምቹ ሁኔታ ተቃዋሚዎች ሊጠቀሙበት አለመቻላቸው ደግሞ የሚካድ ሐቅ አይደለምና ወያኔን ለአንዴም ለሁሌም ለማስወገድ የሕዝብ ጎራን ድክመት ለማብቃት ቁርጥ ያለ እርምጃ መወሰድ አለበት።

ወያኔ በከፍፍልና ዘረኛ ፖለቲካው አመርቂ ውጤት ያገኘው ተቃዋሚና ሀገር ወዳድ የተባለውን ጎራ መከፋፈሉ፤ መበጥበጡና ማዳከሙ ነው። ከነገረ ቀደሙ የግንጠላ አቅዋሙን የቀየረ ለማስመሰል ኢሕአዴግ የሚል ጭንብል አጥልቆ በርካታ ዜጎችን አደናገረ፤ ከፍፍልም ፈጠረ። ያመኑት ባላመኑት ላይ ቅሬታን ያዙ። በወያኔ የገንዘብ ስጡኝ ዘመቻ በርካታ ዜጎች በወቅቱ ተሳትፈው የኢትዮጵያ ጠላት ለሆነው ኃይል መጠናከር አስተዋጽኦ አድርገዋል። አላወቅንም ነበር ማለትም የሚያዋጣ አልነበረም፡፡ ትግላችን ጸረ-አማራ ነው ይል የነበረውን ወያኔ በተደጋጋሚ ኢሕአፓ በጽሁፍም ሆነ በራዲዮ ሲያጋልጥ መቆየቱ ግልጽ ነው። ኢሕአፓ ወያኔን ጠላት ብሎ የፈረጀው በቅድሚያ ነበርና በዚህ ቡድን ሙልጭልጭነት አልተወናበደም። ወያኔ ለሥልጣን ሲበቃም ከመቅጽበት የጎጥና ብሔረሰብ ቡድኖች እንዲፈሉ ተንቀሳቅሷል። በሱዳን እርዳታ ሶማሊያና ሱዳን የነበሩትን ሳይቀር ገዝቶ ወደ አዲስ አበባ አጓጉዞ የሽግግር ጉባዔ ላለው አጃቢና አጫፋሪ አድርጓቸዋል። ዛሬ ተቃዋሚ ነን የሚሉ ያኔ ግን ከነመለስና ታምራት ጎን የቆሙ፤ በአማራው ላይ ሲዘመት ያጀቡና ሹመት ብጤም የተቀበሉትን ታሪክ የሚረሳቸው አይደለም። በሀገር ወዳድ ድርጅቶች ላይ ወያኔን አጅበው የዘመቱና ለወያኔ ጊዜ ይሰጠው ብለው ትጥቅ ያስፈቱትንም እንዲሁ። እጃቸውን አውጥተው የሽግግሩ ጦር የወያኔ ይሁን ብለው የጮሁትን፤ ሻዕቢያ ድረስ ተጉዘው የፈረደበትን አማራ አውግዘው ማንም ሳይወክላቸው ይቅርታ ጠያቂ የሆኑትስ ጉዶች? ጊዜ ቢያልፍም በአንጎላችን ያስቀመጥነው ታሪካዊ ትዝብት ነው። ወጣም ወረደም ግን ወያኔ ተቃዋሚ ሊባል የሚችለውንም ከፋፍሎ ግቡን ለማራመድ ችሏል። እነኢዴኃቅ--ኢሕአፓን አግዶ፤ ኅብረትና ቅንጅትን ከፋፍሎ ከውድቀት መዳኑን ቢያንስ በ1997 ዓ.ም-ና ቀጥሎ በነበሩት ወቅቶች የተገነዘብነው ነው። ዛሬም ቢሆን ወያኔ ሰርጎ ገቦቹን በየድርጅቶቹ ከቶ፤ በተለይም በውጭ ሀገራት በሰፊው ሰግስጎ፤ የተቃዋሚዎች ኅብረት እንዳይመሰረት፤ የጠራ ግንዛቤ እንዳይኖር የአቅሙን እየሠራ ነው። ብዙ ዜጎች ችላ የሚሉት ሌላው አቢይ ሐቅ ደግሞ ይህን የወያኔ ከይሲ ጥረት ባዕዳን እየደገፉና እየተባበሩ መሆናቸውን ነው። ግንዛቤው ባለመኖሩ ግን የሕዝብ ጎራ እንደሰነፍ አርሶ አደር በረት ክፍት እያደረ ጉዳት በተከታታይ ሲደርስ ቆይቷል። ወያኔ የፈለፈላቸው ተለጣፊዎችና ጎጠኞች ዛሬ ሲታዩ ሚዛናቸው ገለባ ሆኖ ይገኛል። እፍ እፍ ያሉ ገንጣዮችም እርስ በርስ በመከፋፈል ላይ ናቸው። የግል ጥቅምና ሥልጣንን ሲያሳድዱም እዚህም ማጥ እዚያም ረግረግ ውስጥ ሳይቀር ዘው ያሉትም ዛሬ በጭቁኑ ሕዝብ የሚወገዙና ወግዱ የተባሉም ሆነዋል። ያለፈውን ሊመልሱ የሚመኙና ጭራቅ ነፍሰ ገዳይን ከወደቀበት ትቢያ ሊያነሱ የሞከሩትንም ወያኔ ክፍፍል ለማባባስ ቢደግፍም ሕዝብ ግን አንቅሮ ተፍቷቸዋል። ካገለገለ ያውደለደለ ሊባሉ የሚገባቸውም ምሳቸውን እያገኙ ነው።

የገባንበት ዘመነ ግሪምቢጥ፣ 'ብለን ነበር'ን መደጋገም ቢያስገድደንም ኢሕአፓ ከ1967 ዓ.ም. ጀምሮ ከወያኔና ጠባቦች ብቻ ሳይሆን የሀገራችንን ውድቀት ከሚመኙ ሁሉ ተቃርኖ ከባድ መስዋዕትነትን ከፍሏል። ይህን ሐቅ የሚክዱ ግን የራሳቸውን ደቃቅ ሚና የሚደብቁ ሞልተዋል --እንኳን በ1967፣ በ1983ም ወያኔን ልጆቼ ብለው ያቀፉ ወይም የደገፉ--የተሞኙ ወይም በጥቅም የተገዙ--ጥቂቶች አልነበሩም። የብዙ ዓመት ጸረ ወያኔ ቅስቀሳን ያጠቃለለውና በመጋቢት 1981 የወጣው <u>አሳን ወደ ተራራ ዝንጀሮን ወደ ባሕር</u> የሚለው የኢሕአፓ መጽሄት የሚከተለውን አስፍሮ ነበር፤

" ልዩነቶች ነበሩን፤ አሉንም ስንል በደፈናው እንዳልሆነ የምታውቁት ቢሆንም በአጭሩ *(ወያኔዎችን)* ልናስታውሳችሁ እንወዳለን።

> እናንተ የኢትዮጵያ ሕዝቦች በአንድነት መኖር አይችሉም፤ እያንዳንዱ ብሔር ብሔረሰብ የየራሱን ነፃ መንግሥት ማቆም አለበት ስትሉ ማኒፌስቶ/ፕሮግራም/አወጣችሁ።
>
> እኛ ይህ ጎጂና ከፋፋይ የጠባብ ብሄረተኛ አቅዋም ነው ስንል ተቃወምናችሁ።
>
> እናንተ የኢትዮጵያ ህዝቦች በአንድነት ሊታገሉም በአንድነት ሊኖሩ ይችላሉ የሚሉ የሸዋ ትምክህተኛና ተንኮለኛ ምሁሮች ብቻ ናቸው አላችሁ። ቀጠል አድርጋችሁም ሸዋ ትምክህተኛ እንጂ ተራማጅ ምሁር የለውም ከማለታችሁ ሌላ ኢሕአፓ ለመላ ኢትዮጵያ ጭቁኖች ሓርነት እታገላለሁ ማለቱን እንደ ሐጢያት ቆጥራችሁ፡" አባይ ኢትዮጵያ" የሚል ቅፅል ስም ለጥፋችሁበት ታወግዙት ነበረ።
>
> እኛ በበኩላችን ደግሞ የብሔር ጭቆናን ለማስወገድም ሆነ ዴሞክራሲያዊ ኢትዮጵያን ለመመሥረት ሕዝቡ ተባብሮ ታግሏል፤ ይታገላልም አልን። ለመላ ኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ፤ በህዝቦቿ ታፍራና ተከብራ ትልቅ ለምትሆን ኢትዮጵያ መታገል የሚያስወግዝ ሳይሆን የሚያኮራ ተልዕኮ ነው አልናችሁ። በጥቅሉ ሸዋ፣ ትምክህተኛ አማራ፤ ጠላት፤ ወዘተ እያላችሁ የትግራይን ህዝብ በጠባብ ብሔረተኛነት ለመመረዝ የምታደርጉት ጥረትም ጥፋት መሆኑን ገለጽንላችሁ።
>
> ትግራይ ተገንጥሎ ነፃ መንግሥት ያቋቁም፤ ትግላችን ጸረ አማራ ነው ትሉ ስለነበር እንደ ኢሕአፓ ዓይነቶቹን ድርጅቶች በጠላትነት መዝግባችሁ ከትግራይ ዉጡልንን አመጣችሁ። አመቺ ሁኔታ በተፈጠረበትም ጦርነት አውጃችሁ በውጊያ ተሰማራችሁ።
>
> እናንተ በኢትዮጵያ የአለው አቢዩ ቅራኔ የብሔር ቅራኔ ነው ትላላችሁ። እኛ ደግሞ የብሔር ጭቆና ያለና መወገድ ያለበትም ቢሆን ዓቢዩ ቅራኔ ሰፊውን የኢትዮጵያ ህዝብ በሞላ ከፋሽስቱ መንግሥትና ከሶቭየት ጣልቃ ገቦች አቃርኖ የሚገኘው ነው እንላለን።
>
> እናንተ ማርክሳዊ ሌኒናዊ ነን፤ የአልባኒያ ገዢ ፓርቲ አፍቃሪ ነን፤ ኢትዮጵያንም በያዝነው ርዕዩተ ዓለም መሠረት እንቃኛለን አላችሁ፤ ፕሮግራምም አወጣችሁ።

በበኩላችን ደግሞ የሶቭየት ሆነ የኢስፓ፤ የማሌሊትም ሆነ የአልባኒያ ሶሻሊዝም ሀቀኛ ስሙ አምባገነንነትና ኢዴሞክራሲያዊነት ነው፤ አይበጀንም ባይ ነን።

እናንተ ጥንትም ጠባብ ብሔረተኛ አልነበርንም፤ የትግራይ ሕዝብ በጠባብነት ስሜት ተበክሎ ስለነበር በቅስቀሳ ለወጥነው፤ ኢትዮጵያዊ ነን፤ የምንታገለው ለመገንጠል አይደለም ትላላችሁ ።

እኛ ደግሞ የአብዬን እከክ ለእምዬ ልክክ አይቻልም፤ የእናንተን ጠባብነት በትግራይ ህዝብ ላይ ለማሳበብ በከንቱ አትጣሩ አልናችሁ። እስካሁንም ድረስ በትግራይ ያለው ቅስቀሳችሁ በጸረ-አማራነት የተቃኘ የትግራይ ብሔራዊ ስሜት እንጂ ኢትዮጵያዊነት አለመሆኑን ሁላችንም ስለምናውቅ አትደብቁ እንላለን።

እናንተ የኢሕአፓ አቅዋምና ፕሮግራም አድህሪና ቡርዣ ነው ትላላችሁ።
እኛ ደግሞ የማሌሊት አቅዋምና ፕሮግራም ኢሰፓን በሌላ ስም ቀጣይ መሆኑ አያጠራጥርም ባይ ነን ።”

በደርጅት ጥያቄ በኅብረት ጉዳይ፤ በመድብለ ፓርቲ አስፈላጊነት፣ ...ወዘተ ወያኔ የነበረውን የተሳሳተ አቅዋም በአብዛኛው መልኩ አልደበቀም። ኢሕአፓን ሲወነጅል አቅዋሙን ግልጽ አድርጎ ቆይቷል፤ አማራን አጠፋለሁ አቋሙንም ከአፉ ያጠፋበት ጊዜ የለም። ለወያኔ ኢትዮጵያና አማራ ተወራራሽ ናቸውና ጸረ ኢትዮጵያነቱን በጸረ አማራነት ነው የገለጠው፤ ዛሬም ሐቁ ይህ ነው። ቢያዩኝ እስቃለሁ ካላዩኝ እሰርቃለሁ ዓይነትም ሁናቴ ከተስማማኝ (ማለትም ሥልጣንን እኔ ከጨበጥኩ) አልገነጠልም ካልሆነ ግን እገነጠላለሁ ሲል የባጀውን ወያኔ፣ ገና ከጠዋቱ ማደባየት ሲገባ ኢሕአፓም ለተወሰነ ጊዜ መቻቻል በሚል ተሳስቶ ሌሎችም በረጅሙ ተደናግረው ለእባቡ መርዙን እንዲረጭ ጊዜ ሰጥተውታል። በ1983 ም የተደገመው ይኸው ነው። በአጭሩ የወያኔ ማንነት ድብቅ አልነበረም ምንም እንኳን አቅዋምን ማዘበራረቅና ማደናገር ደደቢታዊ ተሰጥኦው ቢሆንም። የሆዳም ሀገሩ እምብርቱ ሆነና ያለውን ሁኔታ መገንዘብ ያቃታቸው ማየት የተሳናቸውና አልፎም ለወያኔ ቅቤ ጠባሽ ሆነው የተሰለፉ በመሆናቸው ወያኔ እስከ ዛሬ በላያችን ላይ ሊፈነጭ ችሏል።

እነሱ ሲደላቸው እኛ ግን በድህነት እየማቀቅንና እየሞትን ነው። በይበልጥ የከፋው ደግሞ ሀገራችንን ለማጣት ወያኔ አፋፍ ላይ እያደረሰን መሆኑ ነው። ወያኔ አሁንም ቢሆን የመገንጠል እቅዱን ያልተወ በመሆኑና ይህን ከግብ ለማድረስ ደግሞ ኢትዮጵያን ማፈራረሱ ወሳኝ ይሆንበታልና ከመቸውም ጊዜ በከረረ ደረጃ እስላም ክርስቲያን፤ አማራ ኦሮሞ፤ ...ወዘተ እያለ ሊያናክሰንና ሊበታትነን እየተሯሯጠ ነው። አልተኛም ፤ በቅዠቱም እንኳን ቢሆን ኢትዮጵያዊነት አይመጣበትም። ሕዝብን ለማደናገርና ለመበዝበዝ ግን አንዴ ግድብ ወይም ሌላ እሱ ያሻውን እያለ ሳንተኛ ሊያሞኘን ሁሌም እየጣረ ነው ያለው። አፈናውና ዕመቃው ቅንጣትም አልቀነሰም፤ በየማጎሪያው የተጣሉትን አሁንም ስየል እየፈጸመባቸው ነው፤ ፍርድ ቤቱ የፖለቲካ ውሳኔ ማህተም ሆኗል፣ ነጻ መድረኮችንና መገናኛዎችን ከባዕዳን ጋር በመተባበር ክርችም

አድርጎ ዘግቷል፤ በሃይማኖት ተቋማት ላይ ጣልቃ ገብቶ ማተራመሱን በሰፊው ተያይዞታል፤ ብዙሃን ማህበራትን፣ - የመምህራንን፣ የሠራተኖችን፣ የጋዜጠኞችን፣ ...ወዘተ - በራሱ አምሳል ጠፍጥፎ ለመሥራት ባደረገው እመቃ ነፃ ህልውናቸውን አጥፍቷል። ለአቅመ ሄዋን ያልደረሱ ህፃናት ሴቶችን ለአረቦች እያጋዘ ለሲኦል ዳርጓል፤ ሴቶች በሥርዓቱና በጾታቸው የሚደርስባቸውን በደል ለመቋቋም በነፃ የመደራጀት መብታቸውን ዘግቶ በወያኔ ተለጣፊ ካድሬዎች በኩል መብታቸው እንደተከበረ በስማቸው ያስለፍፋል፤ ህፃናት በምግብ እጥረት አካላቸው ባለመዳበሩ በቀላል በሺታዎች በመጋለጥ በአጭሩ እየተቀሰፉ ነው።

የዴሞክራሲ ጮራ ምናልባት መቀሌ ፈንጥቃ እንደሁ እንጂ በኢትዮጵያ ብልጭ ድርግምንም አልሞከረች። ጨለማ ነው የወያኔ አገዛዝ። ደይን። ወያኔ ሲመሠረት ስህተት ኋላም ደግሞ እብደት ነው የሆነው። በ1967 ያልነውን መድገም መደጋገሙ ጆሮአችው ላይ ለተኙትና ህሊናቸውን ለገደሉት ምናልባት የሚጠቅም ሊሆን ቢችልም ቁም ነገሩ የወያኔን ጸረ-ኢትዮጵያ ዕቅድ ማከሸፍ ነው። እኔ ከሄድኩ ሰርዶ አይብቀል አቅዋሙን እውን ለማድረግ ወያኔ ለኢትዮጵያ ለዛሬም ለነገም ፈንጂ በየቦታው አጥምዶላታል። በአካባቢያችንም ጠላቶች ቀፍቅፎልናል፤ ከግብጽ እስከ ደቡብ ሱዳን ድረስ ይተራመሳል። የጥላቻን ፍም እየቆሰቆሰና እያራገበ በኢትዮጵያም ላይ ሆነ በራሱም ላይ የከፉ ጦርነትን ሊቀስቅስ ደፋ ቀና እያለ ነው። አይሁን እንበልና እነወያኔ፤ ኦህዴድ--ኦነግ የሚመኙት ፍጅት ነገ ቢከሰት የወያኔ መሪዎች ያው መፈርጠጥ እንጂ ሌላ አማራጭ አይኖራቸውም። ንጹህ ሕዝብ ግን የሚያልቅበትና ሶማሊያን የመሰለ ሁኔታ ሊፈጠር የሚችልበትን አደጋ በቀላሉ ወደጎን የምናደርገው አይደለም።

ለዚህም ነው የወያኔ ጸረ-ህዝብነትና ጸረ-ኢትዮጵያነት ቅንጣትም ባልተቀየረበት--እንዲያውም በባሰበት፤ ሀሞትን ዋጥ አድርጎና ቀበቶን አጥብቆ ይህን አስከፊ ሥርዓት ወደ መቃብሩ ለመሸኘት መተባባርና መነሳት የሚያስፈልገው። ይህን ግዳጅ ግን ዛሬም አናይም አንቀበልም ብለን--ያውም በ1997-ሑ ምርጫ ጊዜ ታፍሰው የታጎሩት ብዙዎቹ ሳይፈቱ-- ወደ አዲስ የወያኔ መፈንጫ (ምርጫ) ለመግባት መነዳቱ፣ ያውም ደግሞ ያኔ ከተነሱት ጥያቄዎች መካከል መለስተኛ የሆነውን "የምርጫው ሕግ ይሻሻልን" እንኳ ለማንሳት ድፍረቱን ማጣት የሚያስወቅስ ነው። በሰላማዊ ትግል ጀርባም ከወያኔ ጋር በተጨባጭ መሥራትን መደበቅም አያዋጣምና ጉድጓድ ራሱን ወይም በራሱ አፈር አይሞላም ነውና ወያኔ ባመረረ ትግል ካልተሸነፈ ሕዝብ ጠላኝ ብሎ ከሥልጣን ዞር የሚል አይደለም - ወያኔና ሐቅ፤ ወያኔና ይሉኝታ ሆድና ጀርባ ከሆኑ ዓመታት አልፈዋልና!

በሀገር አድን ትግል የወያኔን አገዛዝ እናደባየው!
የግንጠላንም ሴራ እናከሽፍ !!
ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ !!